PUB 195US (9-23) Amharic

# የመታወቂያ እና የነዋሪነት መስፈርቶች ለዩኤስ ዜጎች

ደህንነታቸው የተጠበቁ የመታወቂያ ማስረጃዎች አሰጣጥን በብሔራዊ ደረጃ ለማሻሻል እየተደረገ እንዳለው ጥረት አንድ አካል፣ Pennsylvania፣ ለPennsylvania Driver's License፣ ለለማጅ ፈቃድ ወይም ለመታወቂያ ካርድ (ID) ከሚያመለክቱ የዩኤስ ዜጎች ወይም ከግዛት ውጭ የመንጃ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ካርድ ከግዛት ውጭ ከሚያስተላልፉ የዩኤስ ዜጎች የሚከተሉትን ሰነዶች ይፈልጋል።

**እባክዎ ያስታውሱ፦ REAL ID ምርት ለማግኘት የሚያመለክቱ ከሆነ፣ እባክዎ ለበለጠ መረጃ የPennDOT ድርጣቢያ <u>https://www.dmv.pa.gov/REALID</u> ላይ የሚገኘውን የREAL ID የሚያስፈልጉ ሰነዶች ዝርዝር ይመልከቱ።**

## <u>ለዩኤስ ዜጎች የእድሜ መስፈርቶች</u>

ለንግድ-ላልሆነ መንጃ ፈቃድ የሚያመለክቱ ግለሰቦች እድሜያቸው ቢያንስ 16 ዓመት መሆን አለበት።

ለመታወቂያ ካርድ የሚያመለክቱ ግለሰቦች እድሜያቸው ቢያንስ 10 ዓመት መሆን አለበት።

ለንግድ ያልሆነን መንጃ ፈቃድ ለማስተላለፍ የሚያመለክቱ ግለሰቦች እድሜያቸው ቢያንስ 16 1/2 ዓመት መሆን አለበት።

ለPennsylvania የለማጅ ፈቃድ የሚያመለክቱ ግለሰቦች እድሜያቸው ቢያንስ 16 ዓመት መሆን አለበት።

ከግዛት-ውጭ የለማጅ ፈቃዶች ወደ Pennsylvania መተላለፍ አይችሉም።

ለንግድ-መንጃ-ፈቃድ ለማግኘት ወይም ለማስተላለፍ የሚያመለክቱ ግለሰቦች፣ በግዛት ውስጥ ለማሽከርከር እድሜያቸው ቢያንስ 18 ዓመት እና ለግዛት ተሻጋሪ ጉዞ ለማሽከርከር ደግሞ እድሜያቸው ቢያንስ 21 ዓመት መሆን አለበት።

## <u>የPennsylvania ነዋሪዎች</u>

እድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ እና የPennsylvania ነዋሪ ከሆኑ የሚከተሉትን ማሳየት ያስፈልግዎታል፦

- ❑ አንድ አይነት መታወቂያ ከዝርዝር A፣ እና
- ❑ የማሕበራዊ ደህንነት ካርድ ( Social Security Card)

እድሜዎ 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነና የPennsylvania ነዋሪ ከሆኑ የሚከተሉትን ማሳየት ያስፈልግዎታል፦

- ❑ አንድ አይነት መታወቂያ ከዝርዝር A፣
- ❑ ከዝርዝር B ደግሞ ሁለት አይነት የነዋሪነት ማስረጃ፣ እና
- ❑ የማሕበራዊ ደህንነት ካርድ

## <u>አዲስ የPennsylvania ነዋሪዎች</u>

ከሌላ የዩናይትድ ስቴትስ ግዛት የሚያገለግል የመንጃ ፈቃድ የያዙ አዲስ የPennsylvania ነዋሪዎች ወደ PA ከገቡ በኋላ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ የPennsylvania መንጃ ፈቃድ ማግኘትና ከግዛት ውጭ ያገኙትን የመጃ ፈቃድ/መታወቂያ ካርድ ማስረከብ አለባቸው።

አዲስ የPennsylvania ነዋሪ ከሆኑና ቀድመው የነበሩበት ግዛት የመንጃ ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜው ከስድስት ወራት በላይ በፊት ያበቃ ከሆነ፣ ወይም ቀድመው በነበሩበት ግዛት መንጃ ፈቃድ ያልነበረዎ ከሆነ የPA የለማጅ ፈቃድ ማመልከት እና የዕይታ፣ እውቀት እና የመንገድ ፈተናዎችን መውሰድ ይጠበቅብዎታል።

የሚያገለግል የፑዌርቶ ሪኮ፣ የዩኤስ ግዛት ወይም በዩኤስ ባለቤትነት ያለው መንጃ ፈቃድ የያዙ አዲስ የPennsylvania ነዋሪዎች የሚያገለግል መንጃ ፈቃዳቸውን ወደ የንግድ ያልሆነ የPA መንጃ ፈቃድ መቀየር ይችላሉ።

ከሌላ የዩናይትድ ስቴትስ ግዛት የተሰጠ የሚያገለግል የንግድ መንጃ ፈቃድ (CDL) የያዙ አዲስ የPennsylvania ነዋሪዎች ያላቸውን CDL ወደ PA CDL.ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

እድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ እና አዲስ የPennsylvania ነዋሪ ከሆኑ የሚከተሉትን ማሳየት ያስፈልግዎታል፦

- ❑ አንድ አይነት መታወቂያ ከዝርዝር A፣
- ❑ የእርስዎ የማሕበራዊ ደህንነት ካርድ፣ እና
- ❑ ከግዛት ውጭ የተገኘ የመንጃ ፈቃድ እና/ወይም መታወቂያ ካርድ

እድሜዎ 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነና አዲስ የPennsylvania ነዋሪ ከሆኑ የሚከተሉትን ማሳየት ያስፈልግዎታል፦

- ❑ አንድ አይነት መታወቂያ ከዝርዝር A፣
- ❑ ከዝርዝር B ደግሞ ሁለት አይነት የነዋሪነት ማስረጃ፣
- ❑ የእርስዎ የማሕበራዊ ደህንነት ካርድ፣ እና
- ❑ ከግዛት ውጭ የተገኘ የመንጃ ፈቃድ እና/ወይም መታወቂያ ካርድ

## ዝርዝር A፦

**የዩኤስ ዜጎች ተቀባይነት ያላቸው የመታወቂያ አይነቶች፦**

- ❑ የዩኤስ ግዛቶችን ወይም የፑዌርቶ ሪኮን ጨምሮ *(በዩኤስ ሥጣን ባለው የዩኤስ መንግስት ኤጀንሲ ደረቅ ማሕተም ያለው የልደት የምስክር ወረቀት የዩኤስ ያልሆነ የልደት የምስክር ወረቀት ተቀባይነት አይኖረውም)* ***ማስታወሻ፦*** *ከፑዌርቶ ሪኮ የተሰጠ የልደት የምስክር ወረቀት ተቀባይነት ለማግኘት የተሰጠበት ቀን 7/1/10 ወይም ከዚያ በኋላ መሆን አለበት።*
    - *የልደት የምስክር ወረቀት የልደት መዝገብዎ የዩናይትድ ስቴጽ ዜግነት ምስረጃ እንደማይሆን የሚገልጽ ቋንቋ ከያዘ፣ ተጨማሪ ሰነዶች ሊያስፈል ጉ ይችላሉ።*
- ❑ የዩኤስ ዜግነት የምስክር ወረቀት (USCIS ቅጽ N-560 ወይም N-561)
- ❑ ከአገር ውጭ የመወለድ የቆንስላ ሪፖርት (DOS ቅጽ FS-240)
- ❑ የዩኤስ ዜግነት የማግኘት የምስክር ወረቀት (USCIS ቅጽ N-550 ወይም N-570)
- ❑ የሚያገለግል የዩኤስ ፓስፖርት

***ማስታወሻ፦ አገል ግሎት ላይ ያሉ ፓስፖርቶች እና ኦርጅናል ሰነዶች ብቻ ተቀባይነት ይኖራቸዋል። በኦርጅናል ሰነድዎ ላይ ያለው ስም ከአሁኑ ስምዎ ጋር የተለያየ ከሆነ፣ ስሞቹን የሚያዛምድ ሰነድ፣ ለምሳሌ ኦርጅናል የጋብቻ የምስክር ወረቀት፣ የፍች ማስረጃ፣ ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰነድ ማቅረብ አለብዎ።***

## ዝርዝር B፦

**18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አመልካቾች እንደ ነዋሪነት ማስረጃ ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ዝርዝር፦ የነዋሪነት ማስረጃ ሰነዶች ስምዎ እና ኦፊሴላዊ የጎዳና አድራሻ በላያቸው ላይ መኖር አለበት።**

- የUSPS፣ UPS፣ FedEx ወዘተ የፖስታ ቤት ማህተም ያለባቸው የፖስታ መልዕክት/ጥቅል ልጣፎች
- A W-2 ቅጽ/ክፍያ ካርኒ
- የሊዝ ስምምነቶች ወይም የቤት ብድር ሰነዶች
- የአሁኑን ስምዎን እና አድራሻዎን የሚያሳዩ ኦፊሴላዊ የግብር መዝገቦች
- ወቅታዊ፣ የአገልግልግሎት ጊዜው ያላለፈ የPA የመንጃ ፈቃድ ወይም ፎቶ ያለው መታወቂያ ካርድ
- የPA ተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ
- የአውቶ መድን ካርድ
- ስምዎን እና አድራሻዎን የሚያሳይ በኮምፒውተር የመነጨ የፍጆታ ደረሰኝ (ሞባይል ስልክ፣ የኬብል፣ ኤሌክትሪክ፣ ጋዝ አገልግሎት)

***ማስታወሻ፦*** *ከሌላ ሰው ጋር የሚኖሩ ከሆነና በስምዎ የወጣ ምንም ደረሰኝ ከሌለ፣ አሁንም ቢሆን ሁለት የነዋሪነት ማስረጃዎችን ማቅረብ ይጠበቅብዎታል። አንዱ ማስረጃ፣ አብረዋቸው የሚኖሩትን ሰው መንጃ ፈቃዳቸውን ወይም ፎቶ ያለበት መታወቂያ ካርዳቸውን ይዘው ወደ መንጃ ፈቃድ መስጫ ማዕከል አብረዎት እንዲመጡ ማድረግ ነው። በተጨማሪ ለምሳሌ የእርስዎን ስም የያዙ በUSPS፣ UPS፣ FedEx ወዘተ የፖስታ ቤት ማህተም የተደረገባቸው የፖስታ መልዕክት/ጥቅሎችን የመሰሉ እንደ ሁለተኛ የነዋሪነት ማስረጃ የሚያገለግል ነገር ማቅረብ ያስፈልግዎታል። አድራሻው እርስዎ አብረዋቸው ከሚኖሯቸው ሰው አድራሻ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።*

## እባክዎ ያስታውሱ

ሁሉም ሰነዶች ተመሳሳይ ስም እና የልደት ቀን፣ ወይም በሰነዱ ላይ ባሉት መረጃዎች መካከል ያለውን ዝምድና የሚያሳዩ መሆን አለባቸው። በሰነዶች መካከል ዝምድና መኖሩን ማረጋገጥ ካልተቻለ ተጨማሪ ሰነድ ሊጠየቅ ይችላል (ለምሳሌ የጋብቻ የምስክር ወረቀት፣ የስም ለውጥ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ የፍች ማስረጃ፣ ወዘተ)